የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23[rd] Year No.3
ADDIS ABABA 28[th] October, 2016

ደንብ ቁጥር ፫፻፺፪/፪ሺ፱ ዓ.ም
የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……………………………………………ገጽ ፱ሺ፫፻፹

Regulation No.392/2016
Commercial Registration and Licensing Council of Ministers Regulation ……………… --Page 9380

የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፪/፪ሺ፱

## ስለንግድ ምዝገባና ፈቃድ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፯ አንቀጽ ፭ እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፱፻፹/፪ሺ፰ አንቀጽ ፶፪(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፪/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ፡

፩/ "አዋጅ" ማለት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥ ፱፻፹/፪ሺ፰ ነዉ፣

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተሰጡት ትርጓሜዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

Council of Ministers Regulation No. 392 /2016

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR COMMERCIAL REGISTRATION AND LICENSING

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 and Article 52(1) of the Commercial Registration and Licensing Proclamation 980/2016.

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Commercial Registration and Licensing Council of Ministers Regulation No. 392/2016".

### 2. Definitions

In this Regulation:

1/ "Proclamation" means the Commercial Registration and Licensing Proclamation 980/2016;

2/ the definitions provided for under Article 2 of the Proclamation shall apply.

## ክፍል ሁለት

## የንግድ ድርጅት ስም እና የንግድ ስም በንግድ መዝገብ ስለመመዝገብ፣ ስለማሻሻል፣ ስለምትክ ምዝገባ እና ስለስረዛ መስፈርቶች

### ፫. የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ድርጅት ስም ስለማስመዝገብ

የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ድርጅት ስም ለማውጣት የሚቀርብ ማመልከቻ በአዋጁ አንቀጽ ፲፬(፩) የተመለከቱ መረጃዎች በማመልከቻ ቅጹ ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

### ፬. የንግድ ማህበራት የንግድ ድርጅት ስም ስለማስመዝገብ

፩/ የንግድ ማህበራት የንግድ ድርጅት ስም ለማስመዝገብ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

ሀ) የንግድ ድርጅት ስሙን እንዲያፀድቅ የተመረጠው የአንድ አባል የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናውን እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

ለ) ያልፀደቀ የመመስረቻ ጽሁፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ፣

ሐ) ለድርጅታቸው መጠሪያ የመረጡት ሶስት አማራጭ ስሞች፡፡

፪/ መዝጋቢው አካል ባደረገው ማጣራት አመልካች ያቀረባቸው ሶስቱ አማራጭ ስሞች በሌላ ድርጅት የተያዙ ከሆነ ሌሎች አማራጭ ስሞችን እንዲያቀርብ ይደረጋል፡፡

### ፭. የንግድ ስም ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለማውጣት

የንግድ ስም ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የአመልካቹ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፪/ የአመልካቹን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ ባለፉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፫/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ ሁሉም መስራቾች ተስማምተው የሰጡት የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉ እና የወካዩ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም የፀና ፓስፖርት ዋናው እና ፎቶ ኮፒ፣

፬/ የንግድ ምዝገባ እና የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ፎቶ ኮፒ፣

## PART TWO

## REQUIREMENTS FOR REGISTRATION, AMENDMENT, SUBSTITUTION AND CANCELLATION OF NAME OF BUSINESS AND TRADE NAME

### 3. Registration of Sole Proprietor

Application to obtain trade name for sole proprietor shall be submitted by filling the particulars specified under Article 14 (1) of the Proclamation.

### 4. Business Name Registration of Business Organization

1/ Application for registration of business name of a business organization shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

a) original and necessary copies of valid identity card or passport of one of the member chosen to register the name of the business organization;

b) the draft articles and memorandum of association;

c) three alternate names for the business organization.

2/ If the registering body upon examination finds that the three proposed names are already taken by other business organization the applicant shall present other alternative names.

### 5. Trade Name Registration Certificate

Application for issuance of a certificate of trade name shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ original and necessary copies of valid identity card or passport of the applicant;

2/ two passport size photographs taken within six months, which shows the clear identity of the applicant;

3/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney given by all of the founders, copies of valid identity card or passport of the attorney and the manager;

4/ copy of certificate of commercial registration and valid business license;

፭/ የንግድ ስሙን ለረጅም ጊዜ ሲጠቀምበት የቆየ ከሆነ ከአካባቢው አስተዳደር ሲገለገልበት የነበረ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማረጋገጫ ደብዳቤ፡፡

**፮. ስለምትክ የንግድ ስም ምስክር ወረቀት**

ምትክ የንግድ ስም ምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

፩/ የአመልካቹ የፀና መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤

፪/ የአመልካቹን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤

፫/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉ እና የወካዩ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም የፀና ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤

፬/ የተበላሸው የንግድ ስም የምስክር ወረቀት፤

፭/ የንግድ ስም የምስክር ወረቀት የጠፋበት ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማስረጃ፡፡

**፯. የንግድ ስም ምስክር ወረቀት ስለማሻሻል**

የንግድ ስም የምስክር ወረቀት ለማሻሻል ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

፩/ የአመልካቹን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤

፪/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወካዩ እና የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፤

፫/ የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ዋናዉንና ፎቶኮፒ፤

፬/ የንግድ ማህበር የንግድ ስም እንዲሻሻል የተጠየቀ ሲሆን በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ እና ስለመሻሻሉ የሚገልፅ አገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ የታወጀበት መረጃ፡፡

**፰. የንግድ ስም ምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ**

የንግድ ስም የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የአመልካቹን ማንነት በግልጽ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች

5/ letter of confirmation from the local administration that the trade name has been in use for long period of time.

**6. Substitute Certificate of Trade Name**

Application for substitute certificate of trade name shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ original and necessary copies of valid identity card or passport of the applicant;

2/ two passport size photographs taken within six months, which shows the clear identity of the applicant;

3/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary copies of valid identity card or passport of the attorney and the manager;

4/ the damaged certificate of trade name;

5/ evidence issued from appropriate organ, if the certificate of trade name cwas lost.

**7. Requirements for Amending Trade Name Certificate**

Application for amendment of certificate of trade name shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ two passport size photographs taken within six months, which shows the clear identity of the applicant;

2/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary copies of valid identity card or passport of the attorney and the manager;

3/ original and copy of valid business license;

4/ when a request is made to amend trade name of a business organization, authenticated minutes and proof of declaration on a newspaper with wider circulation.

**8. Cancellation of Trade Name Certificate**

Applicant for cancellation of certificate of trade name shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ two passport size photographs taken within six months, which shows the clear identity of the application

፪/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወካዩ እና የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፤

፫/ የንግድ ስም ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤

፬/ የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ዋናዉንና ፎቶኮፒ፡፡

፱. <u>ስለግለሰብ ነጋዴ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት</u>

፩/ የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

ሀ) የአመልካቹን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤

ለ) የአመልካቹ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤

ሐ) አመልካቹ ዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፤

(፩) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፤ ወይም

(፪) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፤ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፤

(፫) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፤

መ) ለንግድ ስራዉ የመደበዉ ካፒታል መጠን መግለጫ፣

ሠ) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፤

ረ) አመልካቹ የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ከተጠቀሱት በተጨማሪ

የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲሁም ቅርንጫፍ የሚኖረው ከሆነ የቅርንጫፍ የሥራ አድራሻ ማረጋገጫ

2/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary copies of valid identity card or passport of the attorney and the manager;

3/ certificate of trade name registration;

4/ original and copy of valid business license;

9. <u>Requirements for Commercial Registration of Sole Proprietor</u>

1/ Application for commercial registration of sole proprietor shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

a) two passport size photographs taken within six months, which shows the clear identity of the applicant;

b) original and necessary copies of valid identity card or passport of the applicant;

c) confirmation of address of the head office and branch offices of the business, if any; and

(1) the title deed, if the house used for business is owned by the applicant; or

(2) a valid and authenticated lease agreement, if the house used for business is leased by the applicant from another lessor or lease agreement document issued by appropriate government body if the house used is owned by the Government;

(3) written confirmation letter of address issued by the local administration, if one of the evidences stated under paragraph (a) or (b) of this sub-article could not be produced;

d) capital allocated for the business activity;

e) certificate of Tax Identification Number (TIN);

f) where the applicant is a foreign investor in addition to specified on this Article his investment license, and address of branch office, if any;

፪/ የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀትን በውክልና አስመዝግቦ ማግኘት የተከለከለ ነው፡፡

፲. <u>የሽርክና ማህበራት እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት</u>

የሽርክና ማህበራት እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የሥራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፪/ የንግድ ማህበሩን ሥራ አስኪያጅ ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፫/ በመመስረት ላይ ያለ ከሆነ በሁሉም መስራች አባላት ተፈርሞ የተሰጠ የውክልና ማረጋገጫ ዋና እና ከዋናው ጋር የተመሳከረ ቅጂ፣

፬/ ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ዋና ቅጅዎች፣

፭/ አመልካቹ የውጭ ሀገር ዜጋ ከሆነ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የተሰጠ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እና የግለሰቡ የታደሰ ፓስፖርት ዋናውና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፮/ በሽርክና ማህበራት እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ውስጥ አባል የሆነ የውጭ ሀገር የሕግ ሰውነት ያለው አካል ከሆነ፣

ሀ) ከተቋቋመበት አገር ሕጋዊ ሰውነት ያገኘበትን ማረጋገጫ ሰነድ፣

ለ) አዲስ በሚቋቋመው ማህበር ውስጥ ለመግባት መወሰኑን የሚያሳይ በአገሩ ሕግ መሠረት የተረጋገጠ ቃለ-ጉባዔ ወይም ደብዳቤ ወይም ተመሳሳይ ሰነድ፣

ሐ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ እና በንዑስ አንቀጽ (፭) መሰረት የሚቋቋም የንግድ ማህበር ቅርንጫፍ የሚከፍት ከሆነ የቅርንጫፍ አድራሻ ማረጋገጫ፣

፯/ አመልካቹ የዋና የሥራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የሥራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፣

ሀ/ ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ
የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ
ወይም

2/ Obtaining certificate of registration of sole proprietor via proxy is prohibited.

10. <u>**Certificate of Commercial Registration of Partnerships and Private Limited Companies**</u>

Application for certificate of commercial registration for partnerships and private limited companies shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ original and necessary copies of valid identity card or passport of the manager;

2/ two passport size photographs taken within six months, which shows the clear identity of the manager;

3/ where the applicant is a business organization under formation original or attested copy of the power of attorney document signed by all founders;

4/ original and copies of memorandum and articles of association of the business organization authenticated by the appropriate organ;

5/ where the applicant is a foreign individual his investment license issued by the pertinent body, valid original and necessary copies of passport of the individual;

6/ where a foreign body corporate is member of a partnership or private limited company:

a) certificate of incorporation issued at the country of formation;

b) a notarized minutes of resolution, letter or other similar decision passed pursuant to the laws of country of formation to join the business organization;

c) investment license;

d) branch office address, where the business organization to be incorporated under this sub-article and under sub-article (5) of this Article is to open branch offices;

7/ statement of the principal business address of applicant and branch offices, if any; and:

a) the title deed, if the house used for
business is owned by the applicant;
or

ለ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፣የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፣

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፣

፰/ የዓይነት መዋጮ በሚኖርበት ጊዜ የመዋጮው ባለቤትነት የንግድ ምዝገባው ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ የሽርክና ማህበሩ ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበሩ እንደሚተላለፍ የሚያረጋግጥ በአመልካቹ የተፈረመ ማረጋገጫ፣

፱/ የአዕምሯዊ ፈጠራ ንብረት መዋጮ በሚኖርበት ጊዜ በሰነዶች አረጋጋጭ የተረጋገጠ ቃለ-ጉባኤ ወይም ተመሳሳይ ሰነድ፣

፲/ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፡፡

## ፲፩. የአክሲዮን ማህበር የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት

የአክሲዮን ማኅበር መሥራቾች የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፣

፩/ የአክሲዮን ማህበሩ ስራ አስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፪/ የአክሲዮን ማህበሩን ስራ አስኪያጅ ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፫/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋናው እና ፎቶ ኮፒ፣ የተወካዩ እና የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፬/ የአክሲዮን ማህበሩ በመመስረት ላይ ያለ ከሆነ በሁሉም መሥራች አባላት ተፈርሞ የተሰጠ የውክልና ማረጋገጫ ዋና እና ከዋናው ጋር የተመሳከረ ቅጂ፣

፭/ በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ዋናና ቅጅዎች፡

b) a valid and authenticated lease agreement, if the house used for business is leased by the applicant from another lessor or lease agreement document issued by appropriate government body if the house used is owned by the Government;

c) written confirmation letter of address issued by the local administration, if one of the evidences stated under paragraph (a) or (b) of this sub-article could not be produced;

8/ where there is contribution in kind, a signed statement by the applicant showing that the contribution he made is to be transferred to the partnership or private limited company within a year after registration is made;

9/ where there is contribution of intellectual property, minute or similar document authenticated by a notary;

10/certificate of Tax Identification Number (TIN).

## 11. Certificate of Commercial Registration of Share Company

Applicant for certificate of commercial registration of Share Company shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ original and necessary copies of valid identity card or passport of the manager;

2/ two passport size photographs taken within six months, which shows the clear identity of the manager of the share company;

3/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney given by all of the founders, photocopies of valid identity card or passport of the attorney and the manager;

4/ where the share company is under the process of formation, an original and attested copy of the power of attorney document signed by all founders;

5/ duly authenticated original and copies of memorandum and articles of association of share company;

፮/ በአክሲዮን ማህበር ውስጥ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ግለሰብ አባል የሚገኝ ከሆነ ከሚመለከተው መስሪያ ቤት የተሰጠ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እና የፓስፖርቱ ዋና እና አስፈላጊ ገጾች ፎቶኮፒ፣

፯/ በአክሲዮን ማህበሩ ውስጥ አባል የሆነ የውጭ ሀገር የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት የሚገኝ ከሆነ፣

ሀ) ከተቋቋመበት አገር ሕጋዊ ሰውነት ያገኘበትን ማረጋገጫ ሰነድ፣

ለ) አዲስ በሚቋቋመው አክሲዮን ማህበር ውስጥ ለመግባት መወሰኑን የሚያሳይ በአገሩ ሕግ እና በኢትዮጵያ የሰነዶች አረጋጋጭ የተረጋገጠ ቃለ-ጉባዔ ወይም ተመሳሳይ ሰነድ፣

ሐ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ እና በንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት የሚቋቋም የንግድ ማህበር ቅርንጫፍ የሚከፍት ከሆነ የቅርንጫፍ አድራሻ ማረጋገጫ፣

፰/ አመልካቹ ዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፣

ሀ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፣ ወይም

ለ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፣ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፣

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፣

፱/ ከተፈረመ የአክሲዮን ሽያጭ ቢያንስ አንድ አራተኛ ገንዘብ ተከፍሎ በዝግ ሂሳብ ለመቀመጡ የባንክ ማስረጃ፣

፲/ የአዕምሯዊ ፈጠራ ንብረት መዋጮ በሚኖርበት ጊዜ በሰነዶች አረጋጋጭ የተረጋገጠ ቃለ-ጉባኤ ወይም ተመሳሳይ ሰነድ፣

፲፩/የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፡፡

6/ where a foreign individual is member of the share company his investment license issued by the pertinent body,original and necessary copies of his valid passport;

7/ where a foreign body corporate is member of the share company:

a) its certificate of incorporation issued at the country of formation;

b) a notarized minutes of resolution, letter or other similar decision passed pursuant to the laws of country of formation and Ethiopia to join the share company under formation;

c) investment license;

d) branch address, where the business organization to be incorporated under this sub-article and under sub-article (6) is to open branch offices;

8/ statement of the principal business address of applicant and branch offices, if any; and:

a) the title deed, if the house used for business is owned by the applicant; or

b) a valid and authenticated lease agreement, if the house used for business is leased by the applicant from another lessor or lease agreement document issued by appropriate government body if the house used is owned by the Government;

c) written confirmation letter of address issued by the local administration, if one of the evidences stated under paragraph (a) or (b) of this sub-article could not be produced;

9/ a bank statement showing that at least one fourth of the par value of the subscribed shares of the company is deposited in a blocked account;

10/where there is contribution of intellectual property, a minute or other similar document authenticated by a notary;

11/certificate of Tax Identification Number (TIN).

**፲፪. የመንግስት የልማት ድርጅት የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት**

የፌደራል ወይም የክልል መንግስታት የልማት ድርጅቶች የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ ድርጅቱ የተቋቋመበት ሕግ፣

፪/ የስራ አስኪያጁ የምደባ ደብዳቤ፣

፫/ የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፬/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉ እና የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፭/ የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፮/ የልማት ድርጅቱ የዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፣

ሀ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፣ ወይም

ለ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፊበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፣ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፣

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፣

፯/ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፡፡

**፲፫. የንግድ እንደራሴ ልዩ የምዝገባ ምስክር ወረቀት**

፩/ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

ሀ/ የንግድ እንደራሴው የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፡

**12. Certificate of Commercial Registration of Public Enterprise**

Application for certificate of commercial registration of Federal or Regional Public Enterprise shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ the law of its establishment;

2/ the letter of appointment of the manager;

3/ original and necessary copies of valid identity card or passport of the manager;

4/ where application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary copies of identity card or passport of the attorney and the manager;

5/ two passport size photographs taken within six months, which shows the clear identity of the manager;

6/ statement of the principal business address of the public enterprise and branch offices, if any; and:

a) the title deed, if the house used for business is owned by the applicant; or

b) a valid and authenticated lease agreement, if the house used for business is leased by the applicant from another lessor or lease agreement document issued by appropriate government body if the house used is owned by the Government;

c) written confirmation letter of address issued by the local administration, if one of the evidences stated under paragraph (a) or (b) of this sub-article could not be produced;

7/ Certificate of Tax Identification Number (TIN).

**13. Special Certificate of Commercial Representative**

1/ Application for Special Certificate of Commercial Representative shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

a) original and necessary copies of valid identity card or passport of the representative

ለ) የእንደራሴውን ማንነት በግልፅ የሚያሳዩ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

ሐ) ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የእንደራሴውና የወካዩ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናውና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

መ) ወካዩ ነጋዴ በተቋቋመበት አገር ወይም በሚሰራበት አገር የተመዘገበ ሕጋዊ ሰውነት ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

ሠ) ለበጀት ዓመቱ ለደመወዝ እና ለስራ ማስኬጃ የሚሆን ቢያንስ ፩፻ሺ (አንድ መቶ ሺ) የአሜሪካን ዶላር አገር ውስጥ በእንደራሴው ስም ለማስገባቱ ከባንክ የተሰጠ ማረጋገጫ፣

ረ) እንደራሴው በወካዩ ነጋዴ በእንደራሴነት የተሾመበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ ማስረጃ ዋና ቅጅ፣

ሰ) አመልካቹ የዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፣

(፩) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፣ ወይም

(፪) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜው ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ውል፣ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ውል፣

(፫) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢው የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፣

ሸ) ወካዩ የንግድ ማህበር ከሆነ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ ሀ - ሰ ከተመለከቱት በተጨማሪ የተረጋገጡ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ወይም ድርጅቱ የተቋቋመበት ተመሳሳይ ሰነድ በኢትዮጵያ ውስጥ በሕግ ስልጣን

ለተሰጠው አካል የተረጋገጠ ማስረጃ

b) two passport size photographs taken within six months, which shows the clear identity of the representative;

c) where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney given by the principal business person, original and necessary copies of identity card or passport of the representative and the principal;

d) proof of registration and legal personality of the principal business organization in the country of its formation or in the country of operation;

e) confirmation of bank that minimum of USD 100,000 (One Hundred Thousands) is deposited in the name of the representative for the operation and salary of the budget year;

f) an authenticated proof of appointment of the representative by the principal business person as its commercial representative;

g) statement of the principal business address of the representative applicant and branch offices, if any; and:

a) the title deed, if the house used for business is owned by the applicant; or

b) a valid and authenticated lease agreement, if the house used for business is leased by the applicant from another lessor or lease agreement document issued by appropriate government body if the house used is owned by the Government;

c) written confirmation letter of address issued by the local administration, if one of the evidences stated under paragraph (a) or (b) of this sub-article could not be produced;

h) where the principal is a business organization, in addition to requirements specified under paragraph (a) to (g) of sub-article (1) of this Article, its original copies of memorandum and article of association or similar documents notarized by legal authorized body in

Ethiopia

ቀ) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፡፡

፪/ የንግድ እንደራሴ የምዝገባ የምስክር ወረቀት በውክልና ማውጣት የተከለከለ ነው፡፡

i) Certificate of Tax Identification Number (TIN).

2/ Obtaining special certificate of commercial representative via proxy registration is prohibited.

## ፲፬. በዓለም አቀፍ ጨረታ አሸናፊ ሆነው የሚገቡ የውጭ አገር የንግድ ድርጅቶች የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት

በዓለም አቀፍ ጨረታ አሸናፊ ሆነው የሚገቡ የውጭ አገር ንግድ ድርጅቶች የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

፩/ የስራ አስኪያጁ ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፪/ የስራ አስኪያጁ ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ የተነሳው ሁለት ፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፫/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉና የስራ አስኪያጁን ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፬/ የማህበሩን ሕጋዊ ሰውነት የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት፣

፭/ ማህበሩ በኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ ለመክፈት መወሰኑን እና ስራ አስኪያጅ ስለመመደቡ የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ ወይም ተመሳሳይ ሰነድ፣

፮/ ጨረታውን ከሰጠው አካል የጨረታ ስምምነት ሰነድና የይመዝገብልኝ የድጋፍ ደብዳቤ፣

፯/ የስራ ቦታ አድራሻ የሚያሳይ ሰነድ፣

፰/ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፡፡

## 14. Certificate of Commercial Registration for International Business Organizations that Enter upon Winning International Bid

Application for certificate of commercial registration of international business organizations that enter upon winning International Bid shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ original and necessary copies of valid passport of the manager;

2/ two passport size photographs taken within six months, which shows the clear identity of the manager;

3/ where application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary copies of identity card or passport of the attorney and the manager;

4/ certificate of proof of legal existence of the business organization;

5/ approved resolution minute or similar document showing that the business organization has decided to open branch office in Ethiopia and assign a manager;

6/ the bid agreement from the bidding body and a support letter of registration requirement;

7/ document of business address;

8/ certificate of Tax Identification Number (TIN).

## ፲፭. በሌሎች ሕጎች እንዲነግዱ የተፈቀደላቸውማህበራት የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት

በሌሎች ሕጎች አግባብ ባላቸው የመንግሥት አካላት የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጣቸው ማህበራት የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ አግባብ ካለው የሴክተር መስሪያ ቤት የተሰጠ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

## 15. Certificate of Commercial Registration of Associations Authorized to engage in business under other Laws

Application for certificate of commercial registration of business organization issued business license by other relevant government organs on the basis of other laws shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ certificate of incorporation of the business organization issued by appropriate sectoral organ;

፪/ ስለሚነግዱበት የንግድ ሥራ ዓይነት፣ የካፒታል ምንጭ እና መጠን፣ ስለትርፍ አጠቃቀም፣ የማህበሩ አስተዳደር እና መሰል ጉዳዮችን ያካተተ አግባብ ካለው የሴክተር መስሪያ ቤት የተሰጠ ደብዳቤ፣

፫/ የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፬/ የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፭/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የስራ አስኪያጁ የፀና የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፮/ አመልካቹ የዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፣ ·

ሀ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፣ ወይም

ለ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜው ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ውል፣ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ውል፣

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢው የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፣

፯/ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፡፡

## ፲፮. የዘርፍ ማህበራት የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት

የዘርፍ ማህበራት የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፣

፩/ የሥራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፪/ የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፫/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ሲሆን የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉና የስራ
አስኪያጁ የፀና የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ኮፒ

2/ proof of the business type, source of capital and amount, profit utilization,administration and management and similar matters issued from the appropriate sectoral organ;

3/ original and necessary copies of valid identity card or passport of the manager;

4/ two passport size photographs taken within six months, which shows the clear identity of the manager;

5/ where application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary copies of valid identity card or passport of the attorney and the manager;

6/ statement of the principal business address of applicant and branch offices, if any; and:

a) the title deed, if the house used for business is owned by the applicant; or

b) a valid and authenticated lease agreement, if the house used for business is leased by the applicant from another lessor or lease agreement document issued by appropriate government body if the house used is owned by the Government;

c) written confirmation letter of address issued by the local administration, if one of the evidences stated under paragraph (a) or (b) of this sub-article could not be produced;

7/ certificate of Tax Identification Number (TIN);

## 16. Certificate of Commercial Registration of Sectoral Associations

Application for certificate of commercial registration of Sectoral Associations shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ two passport size photographs taken within six months, which shows the clear identity of the manager;

2/ original and necessary copies of valid identity card or passport of the manager;

3/ where application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary copies of
valid identity card or passport of the attorney and the manager

፬/ በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የመተዳደሪያ ደንብ ዋና ቅጅ፣

፭/ አመልካቹ የዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፣

ሀ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፣ ወይም

ለ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፣ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፣

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፣

፮/ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፡፡

፲፯. <u>በውጭ አገር የተቋቋሙ የንግድ ምክር ቤቶች የቅርንጫፍ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት</u>

በውጭ አገር የተቋቋሙ የንግድ ምክር ቤቶች የቅርንጫፍ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፣

፩/ ከአገራቸው ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ወይም ኤምባሲዎቻቸው ወይም ከንግድ ምክር ቤቶቻቸው ወይም ከአገራቸው አግባብ ካለው አካል ምዝገባው የተፈቀደ ስለመሆኑ የጽሁፍ ማረጋገጫ፣

፪/ በተቋቋሙበት አገር የተሰጠ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም ተመሳሳይ ሰነድ፣

፫/ ቅርንጫፍ ለመክፈት ያመለከተው ንግድ ምክር ቤት ለሚቋቋመው ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የመደበው ስራ አስኪያጅ ሕጋዊ ደብዳቤ፣

፬/ የንግድ ምክር ቤቱን ስራ አስኪያጅ ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፭/ የአመልካቹ የስራ አድራሻ ማረጋገጫ፣ የኪራይ ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የፀደቀ የኪራይ ዉል፣

፮/ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፡፡

4/ authenticated original copy of articles of association;

5/ statement of the principal business address of applicant and branch offices, if any; and:

a) the title deed, if the house used for business is owned by the applicant; or

b) a valid and authenticated lease agreement, if the house used for business is leased by the applicant from another lessor or lease agreement document issued by appropriate government body if the house used is owned by the Government;

c) written confirmation letter of address issued by the local administration, if one of the evidences stated under paragraph (a) or (b) of this sub-article could not be produced;

6/ certificate of Tax Identification Number (TIN).

17. <u>Certificate of Registration of Branch Office of a Foreign Chamber of Commerce</u>

Application for certificate of registration of branch office of a foreign chamber of commerce shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ written authorization to effect registration issued by Ministry of Foreign Affairs or embassy or chamber of commerce or from appropriate organ of their country;

2/ certificate of incorporation of the Chamber of Commerce or other similar document issued by the country of incorporation;

3/ official letter issued to the manager appointed for the branch Chamber of Commerce to be opened;

4/ two passport size photographs taken within six months, which shows the clear identity of the manager of the Branch Chamber of Commerce;

5/ statement of address; if the house used for business is leased a valid authenticated lease agreement;

6/ certificate of Tax Identification Number (TIN).

## ፲፰. የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማሻሻል

የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማሻሻል ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፪/ የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፫/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉና የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፬/ ማሻሻያው የሚደረገው በማህበሩ መተዳደሪያ እና መመስረቻ ጽሁፍ ላይ ከሆነ የማህበሩ አባላት ማሻሻያ ያደረጉበት የተረጋገጠ ቃለ-ጉባዔ ዋና ቅጅ፣ ማሻሻያው ከካፒታል ጋር የሚያያዝ ከሆነ ወይም የአድራሻ ለውጥ ከሆነ ማሻሻያው የተወሰነበት የተረጋገጠ ቃለ ጉባዔ ዋና ቅጅ እና የአድራሻ ማረጋገጫ፣

፭/ ግለሰብ የሆነ የውጭ ሀገር ዜጋ በነባር የንግድ ማህበር ውስጥ እንዲገባ የሚያደርግ ከሆነ የኢንቨስትመንት ይሁንታ፣

፮/ በነባር የንግድ ማህበር ውስጥ አባል ሆኖ የሚገባው የንግድ ማህበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ዋና ቅጅ፣ የሕጋዊ ሰውነት የምስክር ወረቀት ወይም ተመሳሳይ ሰነድ እና አዲስ በሚቋቋመው ማህበር ውስጥ እንዲገባ ሥልጣን ባለው የማህበሩ አካል መወሰኑን የሚያሳይ አግባብነት ባለው የኢትዮጵያ ሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ ቃለ-ጉባዔ ወይም ደብዳቤ እና እንዲሁም ማህበሩ የውጭ አገር ማኅበር ከሆነ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም አባል ሆኖ አክሲዮን እንዲገዛ የተፈቀደ ደብዳቤ፣

፯/ ማሻሻያው ስለግለሰብ ነጋዴ የስራ አድራሻ ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፡፡

## 18. Amendment of Certificate of Commercial Registration

Application for amendment of certificate of commercial registration shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ two passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the manager;

2/ original and necessary copies of valid identity card or passport of the manager;

3/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary copies of valid identity card or passport of the representative and the manager;

4/ where the amendment is to the memorandum and articles of association, minutes of resolution of the share holders of the business organization to make the amendment; the minutes of resolution of the share holders of the business organization; if the amendment is in relation to capital and address of the organization

5/ investment license, if the amendment allows membership of foreign individual in business organization already established;

6/ where a new member is a business organization its original copies of memorandum and article of association, certificate of incorporation or similar document, a notarized minutes of resolution or letter of its decision by legally authorized body in Ethiopia to join the business organization passed by its authorized organ, if it is a foreign company, investment license or authorization letter issued to buy shares of an existing company;

7/ if the amendment is for change of address of a sole proprietor, evidence verifying such change.

## ፲፱. ምትክ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት

ምትክ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች

## 19. Substitute Certificate of Commercial Registration

Application for substitute certificate of commercial registration shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ two passport size photographs taken with in six months time, which shows clear identity of the manager;

፪/ የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፫/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉና የስራ አስኪያጁ የታደሰ የመታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፬/ የተበላሸውን የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣

፭/ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት የጠፋበት ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማስረጃ፡፡

**፳. ስለ ምትክ የንግድ እንደራሴ ምዝገባ የምስክር ወረቀት**

ምትክ የንግድ እንደራሴ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፣

፩/ የእንደራሴውን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፪/ የእንደራሴው የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፫/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉና እንደራሴው የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፬/ የተበላሸውን የንግድ እንደራሴ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፣

፭/ የንግድ እንደራሴው የምዝገባ ምስክር ወረቀት የጠፋበት ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማስረጃ፡፡

**፳፩. የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ**

የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፪/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉና የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፫/ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ማስረጃ

2/ original and necessary copies of valid identity card or passport of the manager;

3/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary copies of valid identity card or passport of the representative and the manager;

4/ the damaged certificate of commercial registration;

5/ evidence issued from appropriate organ if the certificate of commercial registration is lost.

**20. Substitute Commercial Registration Certificate of Commercial Representative**

Application for substitute commercial registration certificate of a commercial representative shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ two passport size photographs taken within six months time,which shows clear identity of the representative ;

2/ original and necessary copies of valid identity card or passport of the representative;

3/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary copies of valid identity card or passport of the representative and the manager;

4/ the damaged commercial registration certificate of the commercial representative;

5/ evidence issued by appropriate body if the commercial registration certificate of the commercial representative is lost.

**21. Cancellation of Commercial Registration Certificate**

Application for cancellation of commercial registration certificate shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ original and necessary copies of valid identity card or passport of the manager

2/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary copies of valid identity card or passport of the attorney and the manager;

3/ certificate of commercial registration

፬/ የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን ስረዛ ቃለ-ጉባዔ ዋና ቅጅ እና የኦዲት ሪፖርት፣

፭/ በአመልካቹ ወጪ በአንድ ወር ልዩነት ሁለት ጊዜ የአገር አቀፍ ስርጭት ባላቸው ጋዜጦች የወጣ ማስታወቂያ ማስረጃ፣

፮/ ቀደም ብለው የተሰጡ የንግድ ስራ ፈቃዶች ተመላሽ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ እና የንግድ ስም የምስክር ወረቀት ተመላሽ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ማሰረጃ

**፳፪. የንግድ እንደራሴ ምዝገባ ልዩ ምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ**

የንግድ እንደራሴውን ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፣

፩/ የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፪/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ ቆውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉና የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፫/ የእንደራሴው ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣

፬/ ቀደም ሲል የተሰጠው የንግድ እንደራሴው ልዩ የምስክር ወረቀት ተመላሽ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፡፡

## ክፍል ሦስት

## የንግድ ስራ ፈቃድ ስለመስጠት፣ ስለማደስ፣ ስለማሻሻል፣ ስለመተካት እና ስለመሰረዝ

**፳፫. ስለግለሰብ ነጋዴ የንግድ ስራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት**

፩/ የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፣

ሀ) የአመልካቹ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

ለ) የግለሰቡን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

ሐ) የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት

4/ in case of business organization, the minutes of cancellation resolution and audit report must be presented

5/ proof of publication of a notice of cancellation in a widly circulated newspapers twice within a month interval at the expense of the applicant;

6/ evidence showing return of previously issued business license and certificate of trade name.

**22. Cancellation of Commercial Registration of Special Certificate of Commercial Representative**

Application for cancellation of special certificate of commercial representative of commercial registration shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ original and necessary copies of valid identity card or passport of the manager;

2/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary copies of valid identity card or passport of the representative and the manager;

3/ registration certificate of the representative;

4/ evidence showing return of previously issued special certificate of commercial representative.

## PART THREE

## BUSINESS LICENSE ISSUANCE, RENEWAL, AMENDMENT, SUBSTITUTION AND CANCELLATION

**23. Business License for Sole Proprietor**

1/ Application for certificate of business license of sole proprietor shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

a) original and necessary copies of valid identity card or passport of the manager;

b) two passport size photographs which shows clear identity of the applicant taken within six months time;

c) certificate of commercial registration;

መ) አመልካቹ የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ የኢንቨስትመንት ፈቃድ፡

ሠ) አመልካቹ የዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፡

(፩) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፡ ወይም

(፪) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፤ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፡

(፫) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፡

ረ) የንግድ ስራ ፈቃድ የተጠየቀበት የስራ መደብ የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ከሆነ ከሚመለከተው የሴክተር መስሪያ ቤት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፡

፪/ የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ስራ ፈቃድ በውክልና ማውጣት የተከለከለ ነው፡፡

**፳፬. <u>የሽርክና ማህበራት እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት</u>**

የሽርክና ማህበራት እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፡

፪/ የስራ አስኪያጅ ወይም የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም የፀና ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፡

፫/ የንግድ ማህበሩ ስራ አስኪያጅ ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳዉ ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፡

፬/ ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶኮፒ፡

d) investment license, in case of a foreign investor;

e) statement of address if the applicant has principal business address and branch offices, if any, and:

(1) the title deed, if the house used for business is owned by the applicant; or

(2) a valid and authenticated lease agreement, if the house used for business is leased by the applicant from another lessor or lease agreement document issued by appropriate government body if the house used is owned by the Government;

(3) written confirmation letter of address issued by the local administration, if one of the evidences stated under paragraph (1) or (2) of this sub-article could not be produced;

f) certificate of competence issued by appropriate sector, if certificate of competence is required for the category of the business;

2/ Obtaining business license for sole proprietor via proxy is prohibited.

**24. <u>Business License for Partnership and Private Limited Companies</u>**

Application for certificate of business license for Partnership and Private Limited Companies shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ certificate of commercial registration;

2/ original and necessary copies of valid identity card or passport of the manager or the representative;

3/ two passport size photographs which shows clear identity of the manager taken within six months time;

4/ authenticated original copies of memorandum and article of association of the business organization;

፭/ አመልካቹ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ግለሰብ ከሆነ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማረጋገጫ እና የፀና ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገጾች ፎቶኮፒ፣

፮/ በሽርክና ማህበራትና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ውስጥ አባል የሆነ የውጭ ሀገር የሕግ ሰውነት ያለው ከሆነ፣

ሀ) ከተቋቋመበት አገር ሕጋዊ ሰውነት ያገኘበትን ማረጋገጫ ሰነድ፣

ለ) በንግድ ማህበሩ ውስጥ ለመግባት የተወሰነበት ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ-ጉባዔ ወይም ተመሳሳይ ሰነድ፣

ሐ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣

መ) የንግድ ማህበሩ ቅርንጫፍ የሚከፍት ከሆነ የቅርንጫፍ አድራሻ ማረጋገጫ፣

፯/ አመልካቹ የዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፣

ሀ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፣ ወይም

ለ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፣ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፣

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፣

፰/ የንግድ ስራ ፈቃድ የተጠየቀበት የስራ መደብ የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ከሆነ ከሚመለከተው የሴክተር መስሪያ ቤት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፡፡

## ፳፭. <u>የአክሲዮን ማህበር የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማውጣት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፤</u>

የአክሲዮን ማኀበር መሥራቾች የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣

፪/ የስራ አስኪያጅ ወይም የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና

5/ where the applicant is a foreign investor his investment license issued by the pertinent body, vaild original and necessary copies of passport of the manager;

6/ where there are foreign incorporated Partnership or Private Limited Company as shareholder:

a) its certificate of incorporation issued at the country of formation;

b) a notarized minutes of resolution or other similar decision passed by the authorized organ to join the business organization;

c) investment license;

d) branch address, where the business organization is to open branch office;

7/ statement of address if the applicant has principal business address and branch offices, if any, and:

a) the title deed, if the house used for business is owned by the applicant; or

b) a valid and authenticated lease agreement, if the house used for business is leased by the applicant from another lessor or lease agreement document issued by appropriate government body if the house used is owned by the Government;

c) written confirmation letter of address issued by the local administration, if one of the evidences stated under paragraph (a) or (b) of this sub-article could not be produced;

8/ a certificate of competence issued by appropriate sector, if certificate of competence is required for the category of the business.

## 25. <u>Requirements for Business License Cirtificate of Share Company</u>

Application for certificate of business license of Share Company shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ certificate of commercial registration;

2/ original and necessary copies of valid identity card or passport of the manager;

፫/ የአክሲዮን ማህበሩን ስራ አስኪያጅ ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በ ፮ ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳዉ ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፬/ ማመልከቻው የተፈረመው በወኪል ከሆነ በሁሉም መስራች አባላት የተሰጠ የውክልና ማረጋገጫ ሰነድ ዋናው እና የተረጋገጠ ቅጅ፣

፭/ የተረጋገጠ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ዋና ቅጂ፣

፮/ በአክሲዮን ማህበር ውስጥ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ግለሰቦች በሚኖሩበት ጊዜ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኢንቨስትመንት ይሁንታ ማረጋገጫ እና የፀና ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገጾች ፎቶኮፒ፣

፯/ በአክሲዮን ማህበር ውስጥ አባል የሆነ የውጭ ሀገር የሕግ ሰውነት ያለው አካል ከሆነ፣

ሀ) ከተቋቋመበት አገር ህጋዊ ሰውነት ያገኘበትን ማረጋገጫ ሰነድ፣

ለ) በንግድ ማህበሩ ውስጥ ለመግባት የተወሰነበት ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ-ጉባዔ ወይም ተመሳሳይ ሰነድ፣

ሐ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣

መ) የንግድ ማህበሩ ቅርንጫፍ የሚከፍት ከሆነ የቅርንጫፍ አድራሻ ማረጋገጫ፣

፰/ አመልካቹ የዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፣

ሀ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፣ ወይም

ለ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፣ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፣

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፣

3/ two passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the manager;

4/ where the application is submitted by an attorney, an authenticated power of attorney given by all founding members and original and copies of valid identity card or passport of the attorney;

5/ authenticated original copies of memorandum and article of association of the business organization;

6/ if there are foreign investor as shareholder in the Share Company, their investment permit issued by the pertinent body, and valid original and necessary copies of passport

7/ where there is foreign body corporate as members of the Share Company:

a) its certificate of incorporation issued at the country of formation;

b) a notarized minutes of resolution or other similar decision passed by the authorized organ to join the business organization;

c) investment license

d) branch address, where the business organization is to open branch office;

8/ statement of address if the applicant has principal business address and branch offices, if any, and:

a) the title deed, if the house used for business is owned by the applicant; or

b) a valid and authenticated lease agreement, if the house used for business is leased by the applicant from another lessor or lease agreement document issued by appropriate government body if the house used is owned by the Government;

c) written confirmation letter of address issued by the local administration, if one of the evidences stated under paragraph (a) or (b) of this sub-article could not be produced;

፱/ የንግድ ስራ ፈቃድ የተጠየቀበት የስራ መደብ የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ከሆነ ከሚመለከተው የሴክተር መስሪያ ቤት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፡፡

፲/ የአክሲዮን ድርሻ ሰርተፊኬት ናሙና እና የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ፡፡

**፳፮. <u>የመንግስት የልማት ድርጅት የንግድ ሥራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት</u>**

የመንግስት የልማት ድርጅት የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣

፪/ የተቋቋመበት ሕግ፣

፫/ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የምደባ ደብዳቤ፣

፬/ የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፭/ የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፮/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ በድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የተወከለበት ደብዳቤ እና የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፯/ አመልካቹ የዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፣

ሀ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፣ ወይም

ለ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፣ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፣

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፣

፰/ የንግድ ስራ ፈቃድ የተጠየቀበት የስራ መደብ የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ከሆነ ከሚመለከተው የሴክተር መስሪያ ቤት የተሰጠ

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

9/ a certificate of competence issued by appropriate sector, if it is required for the category of the business;

10/ sample certificate of shareholding and internal bylaws.

**26. <u>Certificate of Business License for Public Enterprise</u>**

Application for certificate of business license of Public Enterprise shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ certificate of commercial registration;

2/ the law of its establishment;

3/ the letter of appointment of the manager;

4/ two passport size photographs which shows clear identity of the manager taken within six months time;

5/ original and necessary copies of valid identity card or passport of the manager;

6/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney given by head,original and necessary copies of valid identity card or passport of the attorney and the manager;

7/ statement of address if the applicant has principal business address and branch offices, if any, and:

a) the title deed, if the house used for business is owned by the applicant; or

b) a valid and authenticated lease agreement, if the house used for business is leased by the applicant from another lessor or lease agreement document issued by appropriate government body if the house used is owned by the Government;

c) written confirmation letter of address issued by the local administration, if one of the evidences stated under paragraph (a) or (b) of this sub-article could not be produced;

8/ a certificate of competence issued by appropriate sector, if it is required for the category of the business.

## ፳፯. የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት

የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የእንደራሴው የምዝገባ ምስክር ወረቀት፤

፪/ የእንደራሴውን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤

፫/ የእንደራሴው የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤

፬/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጂ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወካዩ እና የእንደራሴው የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፡

፭ ለበጀት ዓመቱ ለደመወዝ እና ለስራ ማስኬጃ የሚሆን ቢያንስ ፩፻ሺ. (አንድ መቶ ሺ.) የአሜሪካን ዶላር በእንደራሲው ስም በአገር ውስጥ ስለማስቀመጡ ከባንክ የተሰጠ ማረጋገጫ፤

፮/ አመልካቹ የዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፤

ሀ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፡ ወይም

ለ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፡ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፡

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፡

፯/ የንግድ እንደራሴው የሚያከናውናቸው ተግባራት መግለጫ፡

፰/ አመልካቹ የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ የንግድ እንደራሴነት ልዩ የምስክር ወረቀት እንደተሰጠው አግባብ ካለው የመንግስት አካል የመኖሪያ እና የስራ ፈቃድ አውጥቶ ለማቅረብ ግዴታ የገባበት ጽሁፍ ማረጋገጫ፡፡

## 27. Special Certificate of Commercial Representative

Application for special certificate for commercial representative shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ certificate of registration of the representative;

2/ two passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the representative;

3/ original and necessary copies of valid identity card or passport of the representative;

4/ where application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney given by the principal, original and necessary copies of valid identity card or passport of the principal and the representative;

5/ a bank confirmation for deposit of minimum of USD 100,000 (One Hundred Thousands United States Dollar) in domestic bank in the name of the representative for operation and salary expenditure for the budget year,

6/ statement of address if the applicant has principal business address and branch offices, if any, and:

a) the title deed, if the house used for business is owned by the applicant; or

b) a valid and authenticated lease agreement, if the house used for business is leased by the applicant from another lessor or lease agreement document issued by appropriate government body if the house used is owned by the Government;

c) written confirmation letter of address issued by the local administration, if one of the evidences stated under paragraph (a) or (b) of this sub-article could not be produced;

7/ details explanation of the business activities of the representative;

8/ if the applicant is a foreign national, verification showing commitment to obtain residence and work permit from appropriate government body, after the issuance of special certificate of commercial representative.

**፳፰. በዓለም አቀፍ ጨረታ አሸናፊ ሆነው የሚገቡ የውጭ አገር ድርጅቶች የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት**

በዓለም አቀፍ ጨረታ አሸናፊ ሆነው የሚገቡ የውጭ አገር ድርጅቶች የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣

፪/ የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት ፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፫/ የስራ አስኪያጁ ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፬/ የስራ ቦታ አድራሻ መግለጫ፣

፭/ ጨረታውን ከሰጠው አካል የጨረታ ስምምነት ሰነድና የይመዝገብልኝ የድጋፍ ደብዳቤ፡፡

**፳፱. በሌሎች ሕጐች እንዲነግዱ የተፈቀደላቸው ማህበራት የንግድ ሥራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት**

በሌሎች ሕጎች አግባብ ባላቸው የመንግሥት አካላት የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጣቸው ማህበራት ወይም የንግድ ድርጅቶች የንግድ ሥራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣

፪/ የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፫/ የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፬/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉ እና የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፭/ አመልካቹ የዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፣

ሀ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ወይም

**28. Business License for International Business Organizations winning International Bid**

Application for certificate of business license for international business organizations that enter upon winning international bid shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ certificate of commercial registration;

2/ two passport size photographs which shows clear identity of the manager taken within six months time;

3/ original and necessary copies of passport of the manager;

4/ notification of business address;

5/ the bid agreement from the bidding body and a support letter of registration requirment.

**29. Certificate of Business License of Business of Associations Authorized to engage in business under other Laws**

Application for certificate of business license of business organizations and entities issued business license in compliance with other relevant laws by other government organ shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ commercial registration certificate;

2/ two Passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the manager;

3/ original and necessary copies of valid Residence identification card or passport of the manager;

4/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney given by all of the founders, original and necessary photocopies of identification card or passport of the attorney and the manager;

5/ statement of address if the applicant has principal business address and branch offices, if any, and:

a) the title deed, if the house used for business is owned by the applicant; or

ለ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፤ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፤

፮/ የንግድ ስራ ፈቃድ የተጠየቀበት የስራ መደብ የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ከሆነ ከሚመለከተው የሴክተር መስሪያ ቤት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፡፡

## ፴. የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ስለማደስ

የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማደስ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የግብር ክሊራንስ፤

፪/ ማህበር ከሆነ የኦዲት ሪፖርት፤

፫/ የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በ ፮ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፤

፬/ ማመልከቻው በወኪል የሚቀርብ ከሆነ የንግድ ማህበር ሲሆን በሁሉም መሥራች አባላት ተፈርሞ የተሰጠ የውክልና ማረጋገጫ ፎቶ ኮፒ እና የወኪሉ እና የሥራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፤

፭/ አመልካቹ የዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፤

ሀ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፤ ወይም

ለ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፤ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢው የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ ::

b) a valid and authenticated lease agreement, if the house used for business is leased by the applicant from another lessor or lease agreement document issued by appropriate government body if the house used is owned by the Government;

c) written confirmation letter of address issued by the local administration, if one of the evidences stated under paragraph (a) or (b) of this sub-article could not be produced;

6/ a certificate of competence issued by appropriate sector, if it is required for the category of the business.

## 30. Renewal of Certificate of Business License

Application for renewal of certificate of business license shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ tax clearance issued from the concerned authority;

2/ audit report in case of an association;

3/ two Passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the manager;

4/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney given by all of the founders if it is business organization; and original and necessary photocopies of valid identification card or passport of the attorney and the manager;

5/ statement of address if the applicant has principal business address and branch offices, if any, and:

a) the title deed, if the house used for business is owned by the applicant; or

b) a valid and authenticated lease agreement, if the house used for business is leased by the applicant from another lessor or lease agreement document issued by appropriate government body if the house used is owned by the Government;

c) written confirmation letter of address issued by the local administration, if one of the evidences stated under paragraph (a) or (b) of this sub-article could not be produced

## ፴፩. <u>የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ስለማደስ</u>

የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማደስ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የግብር ክሊራንስ፡

፪/ የእንደራሴውን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ ባለፉት ፮ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፡

፫/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ እና የእንደራሴው እና የተወካዩ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፣ ማህበር ከሆነ በማህበሩ ተፈርሞ የተሰጠ የውክልና ማረጋገጫ ፎቶ ኮፒ፡

፬/ አመልካቹ የዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ ፤

ሀ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፡ ወይም

ለ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፡ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፡

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፡፡

፭/ በሚታደስበት በጀት ዓመት ፩፻ሺ (አንድ መቶ ሺ) የአሜሪካ ዶላር በእንደራሴው ስም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባቱ ከባንክ የተሰጠ ማረጋገጫ፡

፮/ የንግድ እንደራሴው የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ ለዘመኑ የታደሰ የስራ እና የመኖሪያ ፈቃድ፡፡

## ፴፪. <u>የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ስለማሻሻል</u>

የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማሻሻል ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

## 31. <u>Renew Special Certificate of Commercial Representative</u>

Applicant for renewal of special certificate of commercial representative shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ tax clearance issued from the concerned authority;

2/ two passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the representative;

3/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, and original and necessary photocopies of identification card or passport of the representative and the principal; and power of attorney given by entity if it is business organization;

4/ statement of address if the applicant has principal business address and branch offices, if any, and:

a) the title deed, if the house used for business is owned by the applicant; or

b) a valid and authenticated lease agreement, if the house used for business is leased by the applicant from another lessor or lease agreement document issued by appropriate government body if the house used is owned by the Government;

c) written confirmation letter of address issued by the local administration, if one of the evidences stated under paragraph (a) or (b) of this sub-article could not be produced;

5/ a bank confirmation for having brought into the country a minimum of USD 100,000 (One Hundred Thousands United States Dollar) for office operation and salary expenditure for the budget year;

6/ if the representative is a foreign national he shall submit a renewed residence and work permit.

## 32. <u>Amendment of Business License Certificate</u>

Application for amendment of certificate of business license shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

፩/ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣

፪/ የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት፣

፫/ ማሻሻያው የሚደረገው በማህበሩ መተዳደሪያ እና መመስረቻ ጽሁፍ ላይ ከሆነ የማህበሩ አባላት ማሻሻያው ያደረጉበት የተረጋገጠ ቃለ-ጉባዔ ዋና ቅጅ፣ ማሻሻያው ከካፒታል ጋር የሚያያዝ ከሆነ በተጨማሪ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማረጋገጫ፣ ወይም የአድራሻ ለውጥ ከሆነ ማሻሻያው የተወሰነበት የተረጋገጠ ቃለ ጉባዔ ዋና ቅጅ እና የአድራሻ ማረጋገጫ፣

፬/ ግለሰብ የውጭ ሀገር ዜጋ በነባር የንግድ ማህበር ውስጥ እንዲገባ የሚያደርግ ከሆነ የኢንቨስትመንት ፈቃዱን፣

፭/ አዲሱ አባል የሕግ ሰውነት ያለው አካል ከሆነ የዚሁ አዲስ አባል የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ዋና ቅጅ፣ የመቋቋሚያ የምስክር ወረቀት ወይም ተመሳሳይ ሰነድ እና አዲስ በሚቋቋመው ማህበር ውስጥ ለመግባት ሥልጣን ባለው የማህበሩ አካል መወሰኑን የሚያሳይ አግባብነት ባለው የኢትዮጵያ ሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ ቃለ-ጉባዔ ወይም ደብዳቤ እና ማህበሩ የውጭ ሀገር ከሆነ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እና አክሲዮን እንዲገዛ በሚኒስቴሩ የተሰጠ ፈቃድ፣

፮/ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማሻሻያ የተጠየቀበት የስራ መደብ ቀደም ብለው በነበሩት ውስጥ ያልተካተተ እና የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ከሆነ ከሚመለከተው የሴክተር መስሪያ ቤት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣

፯/ ማመልከቻው በወኪል የሚቀርብ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም የፀና ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገጾች ፎቶ ኮፒ፣

፰/ የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በ ፮ ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፡፡

፴፫. <u>ስለምትክ የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት</u>

ምትክ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የተበላሸው የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት፣

፪/ የመደበኛ እድሳት ጊዜው ያለፈበት ምስክር ወረቀት ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የግብር ክሊራንስ፣

1/ certificate of commercial registration;

2/ certificate of business license;

3/ where the amendment is to the memorandum and articles of a business organization, original copies of resolution minutes of the share holders of the business organization to make the amendment, similarly minutes of resolution of the share holders of the business organization if amendment is in relation to capital and address of the business organization;

4/ investment permit if a foreign individual is to enter into an existing business organization;

5/ where the new member is a juridical person its original copies of memorandum and article of association, certificate of incorporation or similar document, a notarized minutes of resolution or letter of its decision by pertinent body in Ethiopia to join the business organization as passed by its authorized organ, if it is a foreign company, an investment permit and a permit given by the Ministry to buy the shares of an existing company;

6/ If the sector for which amendment of Business license is sought requires certificate of competence, a certificate of competence issued by the concerned body;

7/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney and original and necessary photocopies of residence identification card or valid passport of the attorney;

8/ two passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the manager.

33. **<u>Substitute Certificate Business License</u>**

Applicant for substitute certificate of business license shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ the damaged Business License certificate;

2/ tax clearance from the concerned authority, if the regular renewal period of the certificate is not lapsed;

፫/ የጠፋበት ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማስረጃ፣

፬/ የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ ባለፉት ፮ ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፣

፭/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ እና የስራ አስኪያጁን እና የተወካዩን የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፣ ማህበር ከሆነ በሁሉም መሥራች አባላት ተፈርሞ የተሰጠ የውክልና ማረጋገጫ ፎቶ ኮፒ፡፡

3/ evidence issued from appropriate organ if the certificate of business license was lost;

4/ two passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the manager;

5/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney given by all of the founders, original and necessary photocopies of valid residence identification card or passport of the attorney and the manager.

## ፴፬. ምትክ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት

ምትክ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የተበላሸውን የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት፣

፪/ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት የጠፋበት ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማስረጃ፣

፫/ የእንደራሴውን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ ባለፉት ፮ ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፬/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ እና የወካዩ እና የንግድ እንደራሴው የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፣ ማህበር ከሆነ በሁሉም መስራች አባላት ተፈርሞ የተሰጠ የውክልና ማረጋገጫ ፎቶ ኮፒ፣

፭/ የመደበኛ እድሳት ጊዜው ያለፈበት ምስክር ወረቀት ከሆነ ከሚመለከተው አካል የግብር ክሊራንስ፡፡

## 34. Substitute Certificate of Special Commercial Representative

Application for substitute certificate of special commercial representative shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ the damaged special certificate for commercial representative;

2/ evidence issued from appropriate organ if the special certificate of commercial representative was lost;

3/ two passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the representative;

4/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney given by all of the founders, original and necessary photocopies of valid residence identification card or passport of the representative and the manager;

5/ tax clearance from the concerned authority if the regular renewal period of the certificate is not lapsed;

## ፴፭. የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ

የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ ቀደም ሲል የተሰጠ እና የሚሰረዝ የንግድ ስራ ፈቃድ፣

፪/ የንግድ ስራ ፈቃድ መሰረዣ የግብር ክሊራንስ፣

፫/ የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ

## 35. Cancellation of Certificate of Business License

Application for cancellation of Certificate of Business License shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ the previously issued business license;

2/ tax clearance to cancel the business license;

3/ Valid original and neccessery photocopies of the identification card or passport of the manager;

፬/ የስረዛው ጥያቄ የቀረበው በወኪል ከሆነ በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የውክልና ማስረጃ፣

፭/ ለንግድ ስራ ፈቃዱ የወሰደው የንግድ ስም ምዝገባ ሰርተፊኬት፡፡

**፴፮. <u>የንግድ እንደራሴ ልዩ ምስክር ወረቀት ስለማስረዝ</u>**

የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማስረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የእንደራሴው ልዩ የምስክር ወረቀት፣

፪/ የንግድ እንደራሴው የገቢ ግብር ክሊራንስ፣

፫/ የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፬/ የስረዛው ጥያቄ የቀረበው በወኪል ከሆነ በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የውክልና ማስረጃ፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**፴፯. <u>የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት</u>**

የሆልዲንግ ኩባንያው ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የሆልዲንግ ኩባንያ ስለመመስረቱ ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ ማረጋገጫ፣

፪/ የሆልዲንግ ኩባንያው የቡድን አባላት የፀና የንግድ ስራ ፈቃድ ዋናው እና ፎቶ ኮፒ፣

፫/ የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ-አስኪያጁን ማንነት በግልጽ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሣው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፣

፬/ የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ-አስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፡፡

**፴፰. <u>የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምዝገባ ምስክር ወረቀት እድሳት</u>**

የሆልዲንግ ኩባንያው ልዩ የምስክር ወረቀትን ለማደስ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

4/ where the application for cancellation is submitted by an attorney; power of attorney authenticated by a notary;

5/ certificate of trade name registration given for the business license.

**36. <u>Cancellation of Special Certificate of Commercial Representative</u>**

Application for the cancellation of Special Certificate of Commercial Representative shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ certificate of registration of the representative;

2/ tax clearance of the special commercial representative;

3/ valid original and necessary copies of identification card or passport of the manager;

4/ where the application for cancellation is submitted by an attorney; power of attorney authenticated by a notary.

## <u>PART FOUR</u>

## <u>Miscellaneous Provisions</u>

**37. <u>Special Registration Certificate of Holding Company</u>**

A holding company shall present the following, along with the application, to obtain special registration certificate:

1/ a notarized certification showing the establishment of a holding company;

2/ the valid business license of the members of the holding company; original and photocopy;

3/ two passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the manager of the holding coordinator company;

4/ original and necessary copies of valid identification card or passport of the manager of the holding coordinator company.

**38. <u>Renewal of the Special Registration Certificate of Holding Company</u>**

The holding company shall present the following, along with the application, to renew the special registration certificate:

፩/ የሆልዲንግ ኩባንያው የቡድን አባላት የፀና የንግድ ስራ ፈቃድ፣

፪/ የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ-አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሣው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፣

፫/ የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ-አስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፣

፬/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የተወካዩ እና የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፡፡

፴፱. <u>ስለሆልዲንግ ኩባንያ ምትክ ልዩ የምዝገባ ምስክር ወረቀት</u>

የሆልዲንግ ኩባንያ ምትክ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የተበላሸውን ልዩ የምስክር ወረቀት፣

፪/ የሆልዲንግ ኩባንያው ልዩ የምስክር ወረቀት የጠፋበት ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማስረጃ፣

፫/ የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ-አስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፣

፬/ የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ-አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሣው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፡፡

፵. <u>የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማሻሻል</u>

የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማሻሻል ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ ከአባላቱ መካከል በማናቸውም ምክንያት ከቡድኑ ሲወጡ ወይም ሌላ አዲስ የቡድን አባል ወደ ቡድኑ ሲገባ በሠነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ፣

~~፪/ የሆልዲንግ ኩባንያው ልዩ የምስክር ወረቀት፣~~

፫/ የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ-አስኪያጁ የፀና የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ

1/ the valid business license of the members of the holding company; original and photocopy;

2/ two passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the manager of the holding coordinator company;

3/ original and necessary copies of valid identification card or passport of the manager of the holding coordinator company;

4/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary photocopies of identification card or passport of the attorney and the manager.

**39. <u>Substitute of Special Registration Certificate of Holding Company</u>**

The holding company shall present the following, along with the application, to substitute the special registration certificate:

1/ the damaged special registration certificate;

2/ evidence issued from appropriate organ if the special registration certificate of the holding company was lost;

3/ original and necessary copies of valid identification card or passport of the manager of the holding coordinator company;

4/ two passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the manager of the holding coordinator company.

**40. <u>Amendment of the Special Registration Certificate of Holding Company</u>**

The holding company shall present the following, along with the application, to amend the special certificate of registration:

1/ a notarized minute certification in case any of the members leave the holding company or in case any new member joins the holding company;

~~2/ special certificate of the holding company;~~

3/ original and necessary copies of valid identification card or passport of the manager of the holding coordinator company;

፬/ የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ-አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሣው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፡፡

**፵፩. የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማስረዝ**

የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማስረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የሆልዲንግ ኩባንያው ልዩ የምስክር ወረቀት፣

፪/ የሆልዲንግ ስምምነት ስለመፍረሱ ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ፣

፫/ የሆልዲንግ ስምምነቱ ስለመፍረሱ አገር አቀፍ ስርጭት ባላቸው ጋዜጦች አንድ ጊዜ የታወጀበት ጋዜጣ፣

፬/ የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ-አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶኮፒ፡፡

**፵፪. ስለጠረፍ ንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት**

የጠረፍ ንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የአመልካቹን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፪/ የአመልካቹ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፫/ አመልካቹ የዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፣

ሀ) ለንግድ ሥራ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፣ ወይም

ለ) ለንግድ ሥራ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፣ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፣

4/ two passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the manager of the holding coordinator company.

**41. Cancellation of the Special Certificate of Registration of Holding Company**

The holding company shall present the following, along with the application, to cancel special certificate of registration of holding company:

1/ special certificate of registration of the holding company;

2/ a notarized minute certification showing the dissolution of the holding company;

3/ proof of notice as regards the dissolution of the holding company published once on a newspaper having nationwide circulation;

4/ original and necessary copies of valid identification card or passport of the manager of the holding coordinator company.

**42. Certificate of Commercial Registration of Border Trade**

Application for certificate of commercial registration of border trade shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ two passport size photographs taken within six months time which shows clear identity of the applicant;

2/ original and necessary copies of valid identification card or passport of the applicant;

3/ statement of address if the applicant has principal business address and branch offices, if any, and:

a) the title deed, if the house used for business is owned by the applicant; or

b) a valid and authenticated lease agreement, if the house used for business is leased by the applicant from another lessor or lease agreement document issued by appropriate government body if the house used is owned by the Government;

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፡፡

፬/ ለንግድ ስራዉ የመደበዉ ካፒታል መግለጫ፣

፭/ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፡፡

**፵፫. የጠረፍ ንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀትስለማሰረዝ**

የጠረፍ ንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የአመልካቹ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፪/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉና የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

፫/ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ማስረጃ፣

፬/ የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን ስረዛ ውሳኔ ቃለ-ጉባዔ ዋና ቅጅ እና የኦዲት ሪፖርት፡፡

**፵፬. ስለጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት**

የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የጠረፍ ንግዱ ከሚካሄድበት የአካባቢ አስተዳደር ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው እና ነዋሪ ስለመሆኑ የሚገልፅ ማረጋገጫ፣

፪/ የጠረፍ ንግድ ሥራ ፈቃድ ለማውጣት በሚመለከተው አካል የጠረፍ ንግድ እንዲነግድ የተፈቀደለት ስለመሆኑ የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፣

፫/ የግለሰቡን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሣው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፣

፬/ የግለሰቡ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፣

፭/ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት

c) written confirmation letter of address issued by the local administration, if one of the evidences stated under paragraph (a) or (b) of this sub-article could not be produced;

4/ notification of capital allotted for the business;

5/ Certificate of Tax Identification Number (TIN).

**43. Cancellation of Certificate of Commercial Registration of Border Trade**

Application for cancellation of certificate of commercial registration for border trade shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ original and necessary copies of valid identification card or valid passport of the applicant;

2/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, valid original and necessary photocopies of identification card or passport of the attorney and the manager;

3/ certificate of commercial registration ;

4/ in case of a business organization, the resolution minutes of cancellation decision and audit report.

**44. Special Certificate of Business License of Border Trading**

Applicant for issuance of special certificate of business license of border trading shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ certification from the area where the border trade is conducted stating that the concerned applicant is of Ethiopian nationality and a resident;

2/ written confirmation of authorization from the concerned authority to engage in border trade activity;

3/ two passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the applicant;

4/ original and necessary copies of valid identification card or passport of the applicant;

5/ certificate of Tax identification Number (TIN);.

፮ [illegible]
አስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ

6/ written verification issued from the area of the business address of the application

## ፵፭. የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ስለማደስ

የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማደስ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ ከሚመለከተው አካል የግብር ክሊራንስ፣

፪/ ከሚመለከተው የአካባቢ አስተዳደር የንግድ ስራው እንዲቀጥል የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣

፫/ የግለሰቡን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፣

፬/ የአመልካቹ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፡፡

## 45. Renewal of the Special Business License Certificate for Border Trading

Application for renewal of special business license certificate of border trading shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ tax clearance issued from the concerned authority;

2/ written support letter issued from the area of the business authorizing the business activity to continue;

3/ two passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the applicant.

4/ original and necessary copies of valid identification card or passport of the applicant;

## ፵፮. ስለ ምትክ ጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት

ምትክ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፣

፩/ የተበላሸውን የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት፣

፪/ ምስክር ወረቀቱ የጠፋበት ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማስረጃ፣

፫/ የመደበኛ ዕድሳት ጊዜው ያለፈበት የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ምትክ የተጠየቀበት ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የግብር ክሊራንስ፡፡

## 46. Substitute Certificate of Special Business License of Border Trading

Application for substitute certificate of special business license for border trading shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ the damaged special business license certificate for border trading;

2/ evidence issued from appropriate organ if the special business license for border trading was lost;

3/ tax clearance from the concerned authority if the substitute special business license for border trading is sought after regular renewal period;

## ፵፯. የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ

የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፣

፩/ የተሰጠ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ፣

፪/ ከሚመለከተው ባለሥልጣን የተሰጠ የግብር ክሊራንስ መረጃ፣

፫/ የአመልካቹ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፡፡

## 47. Cancellation of the Special Certificate of Business License of Border Trading

Applicant for cancellation of special certificate of business license for border trading shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ the special business license for border trading;

2/ tax clearance document issued from appropriate authority;

3/ original and necessary copies of valid identification card or passport of the applicant.

**፵፰. የፍሬንቻይዚንግ ልዩ የምዝገባ ምስክር ወረቀት**

የፍሬንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ በሠነድ አረጋጋጭ የፀደቀ የፍሬንቻይዚንግ ውል ዋናውና የተረጋገጠ ፎቶ ኮፒ፤

፪/ የፍሬንቻይዘሩ (ውል ሰጪ) የተመዘገበበትን ምስክር ወረቀት ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ፤

፫/ የፍሬንቻይዚ (ውል ተቀባይ) የፀና ንግድ ስራ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ፤

፬/ የፍሬንቻይዚ ሥራ-አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፤

፭/ የፍሬንቻይዚ ሥራአስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፤

፮/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፤ የወካዩ እና የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፡፡

**፵፱. የፍሬንቻይዚ ልዩ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለማደስ**

የፍሬንቻይዚ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማደስ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፤

፩/ የፍሬንቻይዚ ልዩ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፤

፪/ የፍሬንቻይዚ ሥራ-አስኪያጁ የፀና ንግድ ስራ ፈቃድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፤

፫/ የፍሬንቻይዚ ሥራ-አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን፤ ያላቸው ፎቶ ግራፎች፤

፬/ የፍሬንቻይዚ ሥራ-አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፤

፭/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፤ የወካዩ እና የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፡፡

**48. Special Registration Certificate of Franchising**

Application for special certificate of commercial registration of franchising shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ a notarized franchising contract and authenticated original and copy of the same;

2/ a notarized registration certificate of the franchiser;

3/ photocopy of the valid trade license of the franchisee;

4/ two passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the franchising manager;

5/ original and necessary copies of valid identification card or valid passport of the franchising manager;

6/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary photocopies of valid identification card or passport of the principal and the attorney.

**49. Renewal of Special Certificate of Registration of Franchising**

Application for renewal of special certificate of franchising registration shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ special certificate of registration of franchising;

2/ the original and copy of the valid business license of the franchising manager;

3/ two passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the franchising manager;

4/ original and necessary copies of valid identification card or passport of the franchising manager;

5/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary photocopies of valid identification card or passport of the principal and the attorney

**፶. ምትክ የፍሬንቻይዚ ልዩ የንግድ ስራ የምስክር ወረቀት**

ምትክ የፍሬንቻይዚንግ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የተበላሸውን የፍሬንቻይዚ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት፣

፪/ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት የጠፋበት ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማስረጃ፣

፫/ የፍሬንቻይዚውን ሥራ-አስኪያጅ ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፣

፬/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወካዩ እና የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፡፡

**፶፩. የፍሬንቻይዚ ልዩ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ**

የፍሬንቻይዚ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡

፩/ የፀደቀውን የፍሬንቻይዘሩን እና የፍሬንቻይዚውን ውል የማፍረሻ ስምምነት ሰነድ፣

፪/ የፍሬንቻይዚ ልዩ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፣

፫/ ማመልከቻው በወኪል የሚቀርብ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወካዩ እና የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶኮፒ፡፡

**፶፪. አምራቾች ወይም አስመጪዎች በችርቻሮ መሸጥ የሚችሏቸው የምርት ወይም የዕቃ ዓይነቶች**

፩/ አምራቾች ወይም አስመጪዎች በችርቻሮ መሸጥ የሚችሏቸው የምርት ወይም የዕቃ ዓይነቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡

ሀ) በሞተር ኃይል የሚሰሩ የማምረቻ ማሽኖች፣

ለ) በሞተር ኃይል የሚሰሩ ተሽከርካሪዎች፣

ሐ) የቢሮ እና የቤት መገልገያ ዕቃዎች፣

መ) የሙዚቃ መሳሪያዎች፣

ሠ) ሶፍትዌር

ረ) ብስክሌቶች

**50. Substitute Certificate of a Special Business License of Franchising**

Application for substitute certificate of special business license of franchising shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ the damaged certificate of special business license of franchising;

2/ evidence issued from appropriate organ if the certificate of special business license of franchising was lost;

3/ two passport size photographs taken within six months time, which shows clear identity of the franchising manager;

4/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary photocopies of valid identification card or passport of the principal and the attorney.

**51. Cancellation of Special Certificate of Registration of Franchising**

Application for cancellation of special certificate of registration of franchising shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

1/ the approved cancellation agreement entered between the franchiser and franchisee;

2/ special registration certificate for franchising;

3/ where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, valid original and necessary photocopies of identity card or passport of the attorney and the principal.

**52. Types of Goods or products that Manufacturers or Importers May Sale through Retail**

1/ The following products or goods may be retailed by manufacturers or importers:

a) motor powered manufacturing machineries;

b) motor powered vehicles;

c) office and household furniture;

d) musical instruments;

e) software;

f) bicycle.

ሰ) አሳንሰር እና የተንቀሳቃሽ ደረጃዎች፣

ሸ) የህክምና መሣሪያዎች፣

ቀ) ለምርምር የሚውሉ ኬሚካሎች፣

በ) ሬንጅ፡፡

፪/ አምራቾች ብቻ በችርቻሮ መሸጥ የሚችሏቸው የምርት ዓይነቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡

ሀ) ዳቦ እና ጣፋጭ ምግቦች፣

ለ) የሲሚንቶ እና የሴራሚክ ውጤቶች፡፡

፫/ ከባህሪያቸው የተነሳ አምራቾች ወይም አስመጪዎች በችርቻሮ ለመሸጥ የሚችሏቸው ሌሎች ምርቶች ወይም ዕቃዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወሰኑ ይሆናሉ፡፡

**፶፫. መመሪያ ስለማውጣት**

ለዚህ ደንብ አፈፃፀም ሚኒስቴሩ መመሪያዎችን ማውጣት ይችላል፡፡

**፶፬. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦችና አሰራሮች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም የተለምዶ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፶፭. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከመስከረም ፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

g) lifts and mobile escalators;

h) medical equipment;

i) chemicals used in research and

j) pitch.

2/ The following products or goods may be retailed only by manufacturers:

a) bread and sweet food;

b) cement and ceramics products and byproducts.

3/ The Council of Ministers may decide other products or goods to be retailed by manufacturers or importers based on the nature of products or goods.

**53. Power to Issuance of Directive**

The Ministry may issue directives for implementation of this Regulation.

**54. Inapplicable Regulations and Practices**

No, regulation or customary practices, inconsistent with this Regulation shall have effect with respect to matters covered in this Regulation.

**55. Effective Date**

This Regulation shall be effective as of September 14, 2016

HAILEMARIAM DESALEGN

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA